Hallo
Basel-Stadt

Kanton Basel-Stadt

# የቤት ውስጥ ጥቃት

ከሚከተሉት ተቋማት እርዳታ ያገኛሉ
የቤት ውስጥ ጥቃት ምን ማለት ነው?
ለጥቃት ፈጻሚዎች እርዳታ
ልጆች
ጾታዊ/ወሲባዊ/ ጥቃት
የመኖሪያ ፍቃድ መብት
በድብቅ ማሳደድ
የግዴታ ጋብቻ እና የሴት ልጅ ግርዛት

# ከሚከተሉት ተቋማት እርዳታ ያገኛሉ

የቤት ውስጥ ጥቃት (Häusliche Gewalt) ማለት በቤተሰብ ውስጥ ወይም በአጋርነት መሃከል የሚያጋጥም ጥቃት ማለት ነው ። በቤት ውስጥ ለሚያጋጥም ጥቃት እርዳታ ማግኘት አስፈላጊ ነው። የተለያዩ ማእከላት መረጃ፣ ምክር አገልግሎት እና ድጋፍ ይሰጣሉ። ይህም ብዙውን ጊዜ ሚስጥራዊ፣ ብዙ ጊዜ ከክፍያ ነጻ እና አስፈላጊ ከሆነም ከአስተርጓሚ ጋር በመተባበር የሚተገበር ነው። እነዚህ ቦታዎች እርዳታ ማግኘት ይቻላል።

## በድንገተኛ አደጋ ጊዜ

በድንገተኛ ጊዜ እርዳታን በተመለከተ ተጨማሪ እንደሚከተለው ( ከሚቀጥለው) መረጃ ማግኘት ይቻላል።

- ፖሊስ፡ 112 / አምቡላንስ፡ 144
- ጥበቃ፣ ምክር እና ልጅ ላላቸው እና ልጆች ለሌላቸው ሴቶች መጠለያ ፡ Frauenhaus በባዝል (24/7)፣ 061 681 66 33፣ www.frauenhaus-basel.ch
- ጥበቃ፣ ምክር እና ልጅ ላላቸው እና ልጆች ለሌላቸው ሴቶች መጠለያ ፡ ለሴቶች እና ለልጆች መኖሪያ ቤት (24/7)፣ 061 302 85 15፣ https://wohnen-frauen-kinder.heilsarmee.ch (DE)
- የህክምና እርዳታ ለሴቶች፡ የሴቶች ክሊኒክ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ድንገተኛ አደጋ (24/7)፣ 061 328 75 00፣ www.unispital-basel.ch/frauenklinik
- የህክምና እርዳታ ለህፃናት፣ ለህጻናት እና ለወጣቶች የህክምና እርዳታ፡ የባዝል ዩኒቨርሲቲ የህጻናት ሆስፒታል የድንገተኛ አደጋ (24/7)፣ 061 704 12 12፣ www.ukbb.ch
- የህክምና እርዳታ፡ የባዝል ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል የድንገተኛ አደጋ ማእከል (24/7)፣ 061 265 25 25፣ www.unispital-basel.ch/notfallzentrum
- በችግር ጊዜ ጣልቃ ገብነት፣ በስነ ልቦናዊ ችግሮች እገዛ፡ የባዝል ዩኒቨርሲቲ የሳይካትሪ ክሊኒኮች የድንገተኛ አደጋ ክፍል (24/7)፣ 061 325 51 00፣ www.upk.ch

## የምክር አገልግሎት

አስተማማኝ ሚስጥራዊ እና የነፃ ምክር አገልግሎት። ተርጓሚ ሊቀርብ ይችላል።

- ለሴቶች፣ ለወንዶች፣ ለልጆች እና ለወጣቶች ምክር፣ እርዳታ እና የገንዘብ ድጋፍ፡ በባዝል፣የተጎጂዎች እርዳታ፣ 061 205 09 10፣ www.opferhilfe-beiderbasel.ch
- የችግር ጣልቃገብነት እና ምክር፡ የካንቶናል ፖሊስ ማህበራዊ አገልግሎት (የቤት ውስጥ ጥቃት የካንቶኖች ፖሊስ መምሪያ)፣ 061 267 70 38
- ስለ አልኮል እና ሱስ ችግሮች የምክር አገልግሎት፡- የጤና ዲፓርትመንት፣ የሱስ መቆጣጠሪያ መምሪያ ክፍል፣ 061 267 89 00፣ www.sucht.bs.ch (DE)
- በተለያዩ ቋንቋዎች ስለ ሱስ ችግሮች የምክር አገልግሎት፡- ፡ የመድብለ ባህላዊ የሱስ የምክር አገልግሎት ማእከል MUSUB, 061 273 83 05, www.mituns.ch
- ማንነትዎን ሳይገልጡ የሚሰጥ የምክር አገልግሎት፡- (በስልክ፣ በቻት እና በኢሜል)፡ እርዳታ ለማግኘት (24/7)፣ ስልክ 143 ይደውሉ፣ www.143.ch ድረ-ገጽ ይጎብኙ፣
- እርዳታ እና የምክር አገልግሎት፡ ለወላጆች፣ ለቤተሰቦች እና ለተንከባካቢዎች፡ የወላጅ የአደጋ ጊዜ ጥሪ (24/7)፣ 0848 35 45 55 (የመደበኛ የቤት ስልክ ታሪፍ)፣ www.elternnotruf.ch ድረ-ገጽ ይጎብኙ፣
- ምክር ለሚፈልጉ ወንዶች መማክርት፡ ባዝል ክልል የወንዶች ጽ/ቤት 061 691 02 02, www.mbrb.ch (DE) የምክር አገልግሎት ዋጋ የሚወሰነው ምክር በሚፈልገው ሰው የገንዘብ ዓቅም ላይ ተመርኩዞ ነው።

## ልጆች እና ወጣቶች

አስቸጋሪ የቤተሰብ ችግር ያለባቸው ህጻናት እና ወጣቶች ወደ ፕሮ ጁቬንቱቴን (Pro Juventute) ቀንም ሆነ ሌሊት በመደወል ማመልከት ይችላሉ። በስልክ፣ በጽሑፍ መልእክት ወይም በኢሜል መነጋገር እና መወያየት ይቻላል።

- ህጻናት እና ወጣቶች ማንነታቸውን ሳይገልጡ በስልክ፣ በውይይት፣ በጽሑፍ መልእክት ወይም በኢሜል እርዳታ ማግኘት ይችላሉ። Pro Juventute: ሚስጥራዊ እና ነፃ ምክር 24/7 በስልክ ቁጥር 147፣ እንዲሁም www.147.ch ድረ-ገጽ መጠቀም ይችላሉ፣

## የሕክምና ዕርዳታ እና ጭብጥ የፎረንሲክ ማረጋገጫዎች

አካላዊ እና ወሲባዊ ጥቃትን በተመለከተ፣ በተቻለ ፍጥነት የዶክተር ምርመራ በቶሎ እንዲያገኙ ይመከራሉ። ምርመራው ሚስጥራዊ ነው። የተጎዳው ሰው ይህን መግለፅ ፍቃደኛ ከሆነ ብቻ ለፖሊስ የሚነገረው ነው። የባዝል ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል በአካልና በፆታዊ ጥቃት ላይ ጉዳት ለደረሰባቸው እና ማስረጃዎችን በማግኘት ላይ ያተኮረ ምርመራ በማድረግ የተዋጣለት ነው። ሌላ ቦታ ሂዶ ህክምና የሚፈልግ ማንኛውም ሰው፣ የጥቃት ምልክቶችን በዝርዝር እንዲመዘግብ ሐኪሙን መጠየቅ አለበት።

- ለሴቶች፡ የሴቶች ክሊኒክ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ለድንገተኛ አደጋ (24/7)፣ 061 328 75 00፣ www.unispital-basel.ch/frauenklinik_, Spitalstrasse 21 ይጠቀሙ፣
- ለወንዶች፡ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ባዝል የድንገተኛ አደጋ ማዕከል (24/7)፣ 061 265 25 25፣ www.unispital-basel.ch/notfallzentrum ይጠቀሙ፣
- በአቅራቢያው በሚገኝ ሆስፒታል የቤተሰብ ዶክተር ልምምድ ወይም ድንገተኛ ሆስፒታል
- ለተጎጂዎች እርዳታ በባዝል፣ 061 205 09 10፣ www.opferhilfe-beiderbasel.ch ይጠቀሙ፣

## ለጥቃት ፈፃሚዎች የምክር አገልግሎት

ሚስጥራዊ እና አስተማማኝ አገልግሎት፣ ከትርጉም ጋር፣

- ለቤት ውስጥ ጥቃት በሚመለከት ማማከር፡- በቤት ውስጥ ጥቃት ለተፈጸመ ግጭት የምክር አገልግሎት፣ 061 267 00 26፣ www.bdm.bs.ch (DE)
- ምክር ለሚፈልጉ ወንዶች መማክርት፡ በባዝል ክልል የወንዶች ጽ/ቤት 061 691 02 02፣ www.mbrb.ch (DE) የምክር አገልግሎት ዋጋ የሚወሰነው ምክር በሚፈልገው ሰው የገንዘብ ዓቅም ላይ ነው።

## ሌሎች የመገናኛ ማዕከላት

"ጥቃት ይቁም" (Halt Gewalt) የተሰኘው ድረ ገጽ የቤት ውስጥ ጥቃት ሌሎች ሊረዱ የሚችሉ ቦታዎችን ይዘረዝራል።
ለምሳሌ፣ በስደት መስክ ላሉ ጥያቄዎች፣ የሱስ ምክር፣ የሕግ ምክር ወይም በአስቸጋሪ የቤተሰብ ሁኔታዎች፣

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/haeusliche-gewalt/diese-stellen-helfen

# የቤት ውስጥ ጥቃት ምን ማለት ነው?

የቤት ውስጥ ጥቃት (Häusliche Gewalt) ማለት በቤተሰብ ወይም ከትዳር አጋር ጋር የሚያጋጥም ሁከት ወይም ብጥብጥ ነው። የቤት ውስጥ ጥቃት አካልን እና ስሜትን ይጎዳል። የቤት ውስጥ ጥቃት የተለያዩ ዓይነት ቅርጾች አሉት። በስዊዘርላንድ የቤት ውስጥ ጥቃት የተከለከለ ነው።

## የቤት ውስጥ ጥቃት ምን ማለት ነው?

የቤት ውስጥ ጥቃት በቤተሰብ ወይም በአጋሮች መካከል የሚያጋጥም ሁከት ነው፦ ባለትዳር በሆኑ ሰዎች ወይም አብረው በሚኖሩ ወይም በነበሩ ሰዎች መካከል የሚጋጥም ጥቃት ነው። አብረው ቢኖሩም ባይኖሩም ጥቃቱ ልዩነት የለውም። በወላጆች እና በልጆች መካከል ወይም በወንድሞች/እህቶች መካከል የሚፈጠር ጥቃት የቤት ውስጥ ጥቃት ነው።
የቤት ውስጥ ግጭት እና ጥቃት ወደ አእምሮአዊ እና ሳይኮሶማቲክ በሽታዎች ሊያመራ ይችላል። በተለይም የህጻናት ጤናማ እና ማህበራዊ እድገት.ላይ ከባድ ተጽዕኖ ያመጣል። በተዘዋዋሪም የቤት ውስጥ ጥቃትበሚፈጸምበት ግዜ ህጻናት በተዘዋዋሪ አደጋ ላይ ስለሚወድቁ ይጎዳሉ።

## ጥቃት የደረሰበት ማነው ?

ሁሉም ሰው በቤት ውስጥ ጥቃት ምክንያት ሊጎዳ ይችላል-ወጣቶች እና አዛውንቶች፣ የስዊስ ፓስፖርት ያላቸው እና የሌላቸው፣ ሀብታም እና ድሃ ቤተሰቦች በአጠቃላይ ሁሉም ሰው ። በስዊዘርላንድ ውስጥ ያሉ ብዙ ሰዎች በቤተሰባቸው ወይም (በቀድሞ) አጋራቸው በዓመፅ ምክንያት ይሰቃያሉ። ተጎጂዎች ራሳቸው እርዳታ ቢፈልጉ ጥሩ ነው።

## የተለያዩ ዓይነት ቅርጾች

የተለያዩ የቤት ውስጥ የቤት ውስጥ የጥቃት ዓይነቶች አሉ። - አካላዊ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ ወሲባዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቃቶች። ብዙውን ጊዜ የተለያዩ የጥቃት ዓይነቶች በአንድ ጊዜ ይከሰታሉ።
ለምሳሌ፡ የማያቋርጥ ስድብ፣ ግንኙነት ማድረግን መከልከል፣ ማሰር፣ መግፋት፣ መቆጣጠር፣ አንድን ሰው ወሲብ እንዲፈጽም ማስገደድ፣ ገንዘብ መንጠቅ፣ አንድን ሰው ቋንቋ እንዳይማር መከልከል እና ልጆችን ችላ ማለት ነው። ማስፈራሪያዎች ጭምር ከቤት ውስጥ ጥቃት ዓይነቶች ውስጥ ይካተታሉ።

## የቤት ውስጥ ጥቃት የተከለከለ ነው

የቤት ውስጥ ጥቃት የተከለከለ ነው። በህግ ያስጠይቃል። ፖሊስ የቤት ውስጥ ጥቃት እንዳለ ካወቀ፣ ጥቃቱ የደረሰበት ሰው ባይፈልግም እንኳን ምርመራ ማድረግ አለበት ።

## ከተጎጂዎች ድጋፍ ምክር አገልግሎት ማእከላት የሚሰጡ ድጋፎች (DE)

የተጎጂዎች ድጋፍ ምክር አገልግሎት ማእከላት (Opferhilfe) በቤተሰቦቻቸው ወይም በቀድሞ አጋራቸው ጥቃት የሚደርስባቸውን ሰዎች ይመክራሉ እናም መረጃም ይሰጣሉ። ይህ እርዳታ ከክፍያ ነጻ ነው። ተጎጂዎች ቀጣዩን እርምጃቸውን ከልዩ ባለሙያው ጋር አብረው ማቀድ ይችላሉ።
የድጋፍ ምክር አገልግሎት ማእከላት ሰራተኞቹ ምስጢርን ይጠብቃሉ። ይህም ማለት ስለሚደረገው ውይይት ለሌላ ሰው ማሳወቅ አይፈቀድላቸውም ማለት ነው። ለፖሊስም እንኳን ቢሆንም ለሌላ አካልት ማሳወቅ አይፈቀድለትም።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/haeusliche-gewalt/was-ist-haeusliche-gewalt

**Hallo
Basel-Stadt**

Kanton Basel-Stadt

# ለጥቃት ፈጻሚዎች እርዳታ

በአካል ወይም በስሜታዊነት የተጎዳ ማንኛውም ሰው ራሱ ሀላፊነቱን መውሰድ እና እርዳታ ማግኘት አለበት። በምክር ውይይት ጊዜ አዲስ የባህሪ ለውጥ መማር ይቻላል።

## እርዳታ የት ማግኘት እችላለሁ?

የቤት ውስጥ ጥቃትን በሚመለከት የሚሰጠው የትምህርት ፕሮግራም ግጭቶችን ያለ ጥቃት እንዴት መፍታት እንደሚችሉ ያስተምራል። የሚሰጠው አገልግሎት አዋቂዎችን ማእከላዊ ያደረገ ነው። የትርጉም አገልግሎትም ይኖራል። በ061 267 44 90 ወይም haeusliche-macht@jsd.bs.ch ላይ መመዝገብ ይቻላል። በነፃ ሳይከፍሉ መሳተፍ ይቻላል።
ተጨማሪ አገልግሎቶች፡-

- የቤት ውስጥ ጥቃት በሚመለከት ስለ ግጭት የምክር አገልግሎት፣ 061 267 00 26፣ www.bdm.bs.ch (DE)
- በባዝል ክልል የወንዶች ቢሮ፣ 061 691 02 02፣ www.mbrb.ch (DE).

የምክር ዋጋ የሚወሰነው ምክር የሚፈልገው ሰው የፋይናንስ አቅሙን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። በፍጥነት የልብን መነጋገር ለሚፈልግ ሰው በተዘረጉ የእርዳታ እጆች (Dargebotene Hand) (በስልክ፣ በጽሑፍ መልእክት፣ በቻት፣ በደብዳቤ) እርዳታ ማግኘት ይችላል። በማናቸውም ሰዓት መስመር ላይ የዕለቱ ተረኛ እንዲሁም ምሽት ላይ ይጠብቆታል።.ስምዎንና ማንነቶን ሳይገልጹ ስለ ችግሩ ማነጋገር ይችላሉ።

- ለእርዳታ የተዘረጉ እጆች የእርዳታ አገልግሎት (24/7) ፣ በስልክ ቁጥር 143፣ www.143.ch ይገኛል።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/haeusliche-gewalt/hilfe-fuer-gewalt-ausuebende-personen

# ልጆች

በቤት ውስጥ ጥቃት የሚደርስባቸው ልጆች እርዳታ ያስፈልጋቸዋል።

## የቤት ውስጥ ጥቃት በልጆች ላይ ሌላ ጠንቅ ያመጣባቸዋል።

ልጆች በቤት ውስጥ የቤት ውስጥ ጥቃት ሲደርስባቸው በእድገታቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድርባቸዋል። ይህ የሚሆነው ልጆች ቀጥተኛ የጥቃት ዓላማ እንኳን ባይሆኑም ነው።
አንዳንድ ልጆች ዝም በማለት ይሰቃያሉ፣ ሌሎች ደግሞ የተለያዩ ምልክቶችን ያሳያሉ። ለምሳሌ፡- በትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ ችግሮች፣ አልጋን ማርጠብ፣ ራስ ምታት፣ የአመጋገብ ወይም የእንቅልፍ መዛባት፣ ከሌሎች ልጆች ጋር የመገናኘት እና የመግባባት ችግሮች ወይም የጠበኝነት ምልክቶችን ያሳያሉ።

## እነዚህ ኤጀንሲዎች ለልጆች ድጋፍ ይሰጣሉ

የጥቃት ሰለባ ለሆኑ ድጋፍ ሰጪ የምክር አገልግሎት ማእከላት (Opferhilfe) ልጆች የቤት ውስጥ ጥቃት ሲደርስባቸው የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ። ስለ ድጋፍ ሰጪ የምክር አገልግሎት ማእከላት ተጨማሪ መረጃ እዚህ ያገኛሉ።
የልጆች እና የወጣቶች አገልግሎት የአስተዳደግ ቢሮዎች KJD (Kinder- und Jugenddienst KJD) የልጆች እና የወጣቶችን ጤናማ እድገት በሚመለከት ልጆች እና ወጣቶች እዚያ እርዳታ ያገኛሉ፣ ለምሳሌ በቤተሰብ ግጭቶች የተነሳ።

## ልጆች ምን ማድረግ ይችላሉ? (DE)

በቤት ውስጥ ጥቃት የሚደርስባቸው ልጆች ከቤተሰብ ውጭ ካለ ሰው ጋር ስለ ጉዳዩ ቢነጋገሩ መልካም ነው። ለምሳሌ፡- ከአስተማሪዎች ፣ ከትምህርት ቤቱ የማህበራዊ ሰራተኞች፣ ከጓደኞቻቸው ወላጆች ወይም ከጎረቤቶች ጋር።
Pro Juventute ቀንና ሌሊት ስልክ መደወል ይቻላል። ስፔሻሊስቶቹ ስለ ውይይቱ ስለ ንግግሩ ለማንም አይናገሩም። እነሱም በደንብ ካዳመጡ በኋላ ለተጎጂዎቹ መፍትሄ እንዲያገኙ እርዳታን ይሰጣሉ። ወደ Pro Juventute የሚደረጉ ጥሪዎች ከክፍያ ነጻ ናቸው። ደዋዮች የግድ ስማቸውን መግለጽ አይጠበቅባቸውም። Pro Juventute በጽሑፍ መልእክት፣በቻት ወይም በኢሜል ማግኘት ይቻላል።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/haeusliche-gewalt/kinder

# ጾታዊ/ወሲባዊ/ ጥቃት

ወሲባዊ ጥቃቶች በቀድሞ አጋሮች እና በባለትዳሮች መካከል ይከሰታሉ። ወሲባዊ ጥቃት የቤት ውስጥ የጥቃት አይነት ነው። ለፖሊስ ሪፖርት ማድረግ ይችላል። ምንም እንኳን ተጎጂው ለፖሊስ ሪፖርት ማድረግ ባይፈልግም፣ ከጥቃቱ በኋላ በፍጥነት የሕክምና ምርመራ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

## የሕክምና እርዳታ

የሴቶች ክሊኒክ ወይም የባዝል የዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል የድንገተኛ ማእከል አስተማማኝ የሆኑ ሚስጥራቸው የተጠበቁ ሕክምናዎችን ያካሂዳል።

- ሀኪሙ ስለ ምርመራው ለማንም አይናገርም።
- ማንኛውም ጥቃት ይመዘገባል። ማስረጃዎቹ ለ1 ዓመታት ያህል ይቀመጣሉ።
- ሰነዶቹ በኋላ ለፖሊስ ሊሰጡ ይችላሉ። ጠቃሚ ማስረጃዎች ናቸው።
- ሀኪሙ ከተጎጂዎች ድጋፍ ስጪ የምክር ማእከላት ጋር በኔት ዎርክ ግንኙነት መፍጠር ይችላል።

## አመጽ ከተፈጸመበት ጊዜ እና በምርመራው ግዜ መካከል ስላለው ሁኔታ (DE)

- ገላቸውን እና እጃቸውን ምንም ነገር መታጠብ የለባቸውም።
- በተቻለ መጠን ወደ መጸዳጃ ቤት መሄድ የለባቸውም።
- ልብሳቸውን ሳያጥቡ ወደ ምርመራው ቦታ ልብሱን ይዘው መምጣት አለባቸው።

## የሕግ እና የስነ-ልቦና ምክር አገልግሎት (DE)

ለተጎጂዎች የምክር አገልግሎት ስጪ ማዕከላት (Opferhilfe) የህግ እና የስነ-ልቦና ድጋፍ ሊሰጡ ይችላሉ። ለብዙ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ይሰጣሉ። እዚህም ተጨማሪ ሌሎች ድጋፎችን ማግኘት ይችላሉ።

## ለፖሊስ ሪፖርት ማድረግ

ጾታዊ ጥቃትን በሚመለከት ፖሊሶች ጥቃት ሪፖርት ሲደረግ የመቀበል እና የመመዝገብ በቂ ተሞክሮ አላቸው። ቃለ መጠይቆች የሚካሄዱት ተመሳሳይ ጾታ ባለው ሰው ነው። ቅሬታው በፖሊስ ጣቢያ ሊቀርብ ይችላል። የሚያምኑትን ሰው ወይም ከተጎጂዎች ምክር ስጪ ማዕከላት ልዩ ባለሙያ ሪፖርት ለማደረግ ይዘው መምጣት ይችላሉ።
ከስራ ሰዓታት ውጪ ፖሊስጋ በአደጋ ጊዜ ስልክ 117 ወይም 112 መደወል ይቻላል።
የካንቶኑ ፖሊስ ማህበራዊ አገልግሎት (Sozialdienst) በቤት ውስጥ እና በፆታዊ ጥቃት ላይ የተለየ ሙያዊ ዕውቀት አላቸው።

- የካንቶኑ ፖሊስ ማህበራዊ አገልግሎት ስልክ ቁጥር 061 267 70 38 (በቢሮ የስራ ሰዓት)

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/haeusliche-gewalt/sexualisierte-gewalt

# የመኖሪያ ፍቃድ መብት

በግል ምክር ማግኘት አስፈላጊ ነው! ከተጎጂዎች ምክር አገልግሎት ስጪ ማዕከላት (Opferhilfe) ጋር መነጋገር የመኖሪያ መብትን ወደ ማጣት አያመራም። ውይይቱ አስተማማኝ እና ሚስጥራዊ ነው። የተጎጂዎች ምክር አገልግሎት ስጪ ማዕከላት ስለ ውይይቱ ለማንም አይናገሩም።

## በቤት ውስጥ አመጽ ምክንያት ከመለያየት በኋላ የመኖሪያ ፍቃድ መብት (DE)

አንድ ሰው በትዳር ላይ ተመስርቶ በስዊዘርላንድ ውስጥ የሚኖር ከሆነ እና የቤት ውስጥ ጥቃት ቢያጋጥመው፣ ይህ ሰው ከመለያየት በኋላም ቢሆን እንደ ሁኔታው ስዊዘርላንድ ውስጥ በቀጣይነት ሊኖር ይችላል። እያንዳንዱ ሁኔታ የተለየ ነው። ለዚህም ነው የምክር አገልግሎት ማግኘት አስፈላጊ የሚሆነው።
የተጎጂዎች ምክር አገልግሎት ስጪ ማዕከላት (Opferhilfe) ድጋፍ ሊሰጡ ይችላሉ። ስፔሻሊስቱ/ ባለሙያው/ በወቅቱ ያለውን የህግ ሁኔታ ያብራራል እና ለተጎጂው በቀጣይ ደረጃዎች ድጋፍ ይሰጣል። የምክር አገልግሎቱ ከክፍያ ነጻ አስተማማኝ እና ሚስጥራዊ ነው። አስተርጓሚም ሊቀርብ ይችላል።

## ጥቃትን መዝግቦ መያዝ

ጥቃት እንደተፈፀመ ለማረጋገጥ የማስረጃ መኖር በጣም አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ፡ የጉዳት ማረጋገጫ ፎቶዎች፣ የዛቻ ወይም የጥቃት ስክሪን ሾት ምስሎች በኋትስ- አፕ፣ በፌስ-ቡክ እና ሌሎችም ማስረጃዎች ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ መቀመጥ አለባቸው። ለምሳሌ፣ በጓደኛ ቤት ወይም በሥራ ቦታ።
በተጓዳኝም አንዳንድ በአካባቢው የሚገኙ ሰዎች ስለ ጥቃቱ ቢያውቁ መልካም ነው። ለምሳሌ፣ ጓደኛ፣ የስራ፣ የሰፈር ወይም የትምህርት ቤት ሰው ቢያውቅ ጥሩ ነው።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/haeusliche-gewalt/aufenthaltsrecht

# በድብቅ ማሳደድ

በድብቅ ማሳደድ የጥቃት ዓይነት ሲሆን በጣም አስጨናቂም ነው። ስለጉዳዩ ማውራት እና ምክር ማግኘት አስፈላጊ ነው።

## በድብቅ ማሳደድ ምንድን ነው?

በድብቅ ማሳደድ ከልክ በላይ አፍጥጦ መመልከት፣ መገናኘት፣ ክትትል ማድረግ እና ሰውን ማስጨነቅ ማለት ነው። ይህ የሚደረገው ከሚሳደደው ሰው ፍላጎት ውጭ በድብቅ ነው። አብዛኛውን ግዜ ይህን የሚያደርጉ ጥቃት ፈጻሚዎች የተጠቂው (የቀድሞ አጋሮች) የቅርብ ሰዎች ወይም እንግዳ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ።
ለምሳሌ፡- ብዙ ቁጥር ያላቸውን የጽሑፍ መልእክቶችን፣ ኢሜይሎች እና ሌሎች መልዕክቶችን መላክ፣ በሥራ ቦታ ወይም በቤት ውስጥ አድፍጦ መሰለል፣ በስልክ ሽብር መፍጠር፣ ያልተፈለጉ ስጦታዎችን መስጠት እና ስለ ግለ ሰቡ ከሚያውቁ ሰዎች አካባቢ መረጃ መፈለግ።
ተደብቆ ማሳደድ በተጎጂው ጤና ላይ አካላዊ እና ስነ ልቦናዊ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል።

## ጥቃትን መዝግቦ መያዝ

በድብቅ የማሳደድ ተግባሩን በሚመለከት ማረጋገጫ መያዝ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ፣ የጥቃቱ ሰለባ የሆነው ግለሰብ ስለ እያንዳንዱን የማሳደድ ድርጊቶች በሚመለከት ማስታወሻ መያዝ (ለምሳሌ ስጦታዎች፣ ማስታወሻዎች፣ የስልክ ጥሪዎች)፣ ተጎጂዎች በአካባቢያቸው ላሉ ሰዎች (ጎረቤቶች፣ ጓደኞች ወይም አሰሪ) ማሳወቅ እና የማንኛውም መልእክት ቅጽበታዊ ገጽ እይታዎችን/ፎቶዎችን ማንሳት ይችላሉ (ኋትስ-አፕ፣ ፌስ-ቡክ ወዘተ)።

## እርዳታ ፍለጋ

የተጎጂዎች ምክር አገልግሎት ስጪ ማዕከላት (Opferhilfe) ድጋፍ መስጠት ይችላሉ። ስፔሻሊስቶች ስለ ህግ ሁኔታው ማብራሪያ መስጠት እና ተጎጂውን በቀጣይ እርምጃዎች መደገፍ ይችላሉ።
የካንቶኑ ፖሊስ ማህበራዊ አገልግሎት ዘርፍ (Sozialdienst) ተደብቆ በማሳደድ ጥቃትን በሚመለከት ላይ ልዩ የሆነ ዕውቀት አላቸው። የጥቃት ሰለባው የሆኑ ሰዎች ከማህበራዊ አገልግሎት ዘርፉ ጋር ግንኙነት ማድረግ ይችላሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/haeusliche-gewalt/stalking

# የግዴታ ጋብቻ እና የሴት ልጅ ግርዛት

በስዊዘርላንድ ውስጥ የግዳጅ ጋብቻ (Zwangsheirat) እና የሴት ልጅ ግርዛት (Mädchenbeschneidung) የተከለከለ ነው። በተጓዳኝም ልዩ ስልጠና ከወሰዱ ባለሙያ ማዕከላት በተጨማሪ የተጎጂዎች ምክር ስጪ ማዕከላት ድጋፍ ይሰጣሉ።

## በግዴታ ጋብቻ ማለት ምን ማለት ነው?

አንድ ሰው በቤተሰቡ ግፊት እና ከራሱ ፍላጎት ውጭ ሌላ ሰው እንዲያገባ ሲገደድ ይህም የግዴታ ጋብቻ ይባላል። ጋብቻው በህግ ቅቡልነት የሌለው እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል። ሰዎች በትዳር ውስጥ በፍቃዳቸው ለመቆየት ወይም ለመለያየት የመምረጥ ነፃነት አላቸው። አንድ ሰው በትዳር ውስጥ ያለ ፍቃዱ ከኖረ የግዴታ ጋብቻ ነው ተብሎም ይጠራል።
የማስገደድ ምሳሌዎች፡- ማስፈራሪያዎች፣ ጥቁረች፣ የስነ ልቦና ጫና ወይም አካላዊ ጥቃትን ያካትታል።
በስዊዘርላንድ የግዳጅ ጋብቻ የተከለከለ ነው።

### እገዛ

የብሔራዊ የስፔሻሊስት ክፍል 'zwangsheirat.ch' ለተጎጂዎች እና ለባለሙያዎች ሚስጥራዊ ምክሮችን በነጻ ይሰጣል፡ የእርዳታ መስመር በ0800 800 007 ወይም በኢሜል info@zwangsheirat.ch ይገኛል።

## የልጃገረዶች ግርዛት ማለት ምን ማለት ነው? (DE)

በሴት ልጅ ግርዛት ወቅት፣ የሴትዋ የብልት አካል ይቆረጣል። የተለያዩ የአገራረዝ ዓይነቶች እና ልምዶች አሉ። የተገረዙ ልጃገረዶች እና ሴቶች ብዙውን ጊዜ በጤና እና በስነ-ልቦናዊ ችግር ይሠቃያሉ።
የሴት የብልት አካል መቁረጥ (መግረዝ) በህግ የተከለከለ ነው። ወላጆች የልጃቸውን መገረዝ ከስዊዘርላንድ ውጭ ካደራጁ ክስ ሊመሰረትባቸው ይችላል።

### እገዛ

የሴት ብልት አካልን መገረዝ የሚቃወመው ኔትዎርክ /መረብ/ (Netzwerk gegen Mädchenbeschneidung) ወሳኝ ከሆኑ ቁልፍ ሰዎች ጋር መረጃ እና አውታረ መረቦችን ያቀርባል። ካሪታስ ስዊዘርላንድ የተጎዱ ቤተሰቦችን በነጻ እና በሚስጥር የምክር አገልግሎት ይሰጣል። 042 419 23 55 / beratung@maedchenbeschneidung.ch
የተጎጂዎች ምክር አገልግሎት ስጪ ማዕከላት (Opferhilfe) ድጋፍ ሊሰጡ ይችላሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/haeusliche-gewalt/zwangsheirat-und-maedchenbeschneidung